የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት

THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA

HIS IMPERIAL HIGHNESS PRINCE ERMIAS SAHLE-SELASSIE HAILE-SELASSIE
PRESIDENT

# ዕርቅ እንዲሁም
# ብልጽግና ፣ እኩልነትና ተስፋን መገንባት

ሰኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም.

**መግለጫ**

## ከልዑልነታቸው ልዑል ኤርሚያስ ሣኅለ-ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ
## የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት ሊቀ መንበር

በዘውድ ምክር ቤታችን ሥም የታዋቂውን ዘፋኝ የአቶ ሀጫሉ ሁንዴሳን ሞት አስመልክቶ ለቤተሰቦቹ የተሰማንን ጥልቅ ሃዘን ለመግለጽ እንወዳለን ። አቶ ሀጫሉ በሙዚቃ ስራ ለኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ አስተዋጾ ያበረከተ ፣ ለኦሮሞ ባህል ያለውን ፍቅር ያስመሰከረና የአንድነትን ጥቅምና ዋጋ በተቀጣይነት እንድናሰላስልና እንድንመረምር አድርጎናል ። በኢትዮጵያና በዓለም ዙሪያ ለምንኖር ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የአቶ ሀጫሉ አሰቃቂና ግድያ መራር ሀዘን ሆኖብናል ። ሕይወቱ ባጭሩ በመቀጨቱ ሁላችንም ከልብ አዝነናል።

መላው ዓለም በተለያዩ ማህበራዊ እክል በተወጠረችበት ወቅት ፣ የዓለም የጤና ቀውስ (ወረርሽኝ) ያስከተለው የዓለምን ኢኮኖሚና የብሔሮች ደህንነትን ማናጋት ጋር ተጨማሪ የደፋር ሰው ሕይወት ማጣት ለሀዘን ዳርጎናል ። በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች የጥላቻ ወንጀሎች በሁሉም ማህብረሰቦች ተከስተዋል፣ ገንፍለውም ወጥተዋል ። የጥላቻ ወንጀል ማህብረሰባዊ ቀውስ በመፍጠር ጥቂት ሴረኛና አፍራሽ ሃይሎችን ተጠቃሚ ሲያደርግ የተቀረውን ሕዝብ የሚያተራምስና ብዙሃኑን በፍራቻ ቆፈን የሚማግድ ነው።

ልዩነቶቻችንን የምንፈታበትና ወደ ዕርቅ የምናመራበት ሰዓት አሁን ነው። እያንዳንዳችን ሰክነን የምናስብበትና ወደ ህሊናችን የምንመለስበት ጊዜ ነው። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ፣ በተሳሳተ ጎዳና የሚሄዱትን ወደ ትክክለኛው መንገድ የምንመልስበትና ኢትዮጵያን ለማበልጸግ ፣ ሠላምና አንድነቷን ለማስከበር እናትና አባቶቻችን የነበራቸውን በጎ ምኞትና ተስፋ እውን ለማድረግ ለልጆቻችንና ለተተኪው ትውልድ ስንል ሁላችንም በመተባበር ጠንክረን መስራት አለብን።

ታሪክን ቀይሮ መጻፍ ወይም ከተከናወነበት አውድ ውጭ ማቅረብና በጎ ላልሆነ ዓላማና ድርጊት ማዋል አደገኛ አካሄድ ነው ። ሚዛኑን በጠበቀ ሁለንተናዊ የታሪክ ትምህርት ለመማር ወጣቱ ትውልድና ልጆቻችን አልታደሉም ። ቢታደሉ ኖሮ በተባበረ ክንድና ሕዝባዊ አንድነት አፍሪካን በመምራት ለመላው ዓለም በአርአያነት ኢትዮጵያ ያሳየችውን አገራዊ ልዕልናና የአንድነት ጥንካሬ ይረዱ ነበር ። የኢትዮጵያችን ታላቅነት በዘውግ ላይ ተመስርቶ አያውቅም ። የኢትዮጵያ ክብርና

ታላቅነት ምን ጊዜም ሲገለጽ የኖረው አገራችን ውስጥ በነበሩት የተለያዩ የአንድ ሉዓላዊ አገር እህትማማችና ወንድማማች ቤተሰብ መንፈስ ፣ እምነትና ባህል ነው።

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ካኒዛሮ መናፈሻ ዊምበልደን በተባለ አካባቢ በእንግሊዝ ሀገር ዋና ከተማ ሎንደን ላይ የነበረውን የግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴን ሐውልትና በኢትዮጲያ በሐረር ከተማ የነበረውን የግርማዊነታቸውን አባት የልዑል ራስ መኰንንን ሐውልት የማፍረስ ተግባርና ወንጀለኛ ድርጊት እጅግ የሚያሳዝን እኩይ ተግባር ነው ። የአገራችንን ሠላምና አንድነት በተቀጣይነት እንዲጠበቅ ልዑል ራስ መኰንንና ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ በኢትዮጵያና በሕዝባችን መጻኢ ዕድል የነበራቸው ሥጋት ያገራችን የውስጥ አፍራሽ ኃይሎች እስከዛሬዋ ዕለት ድረስ ባደረሱት የሀገር ክህደት ወንጀልና ጥቃቶች ሁሉ እውነትና ተገቢ እንደነበር ያረጋግጣል።

በሀገራችንና በመላው ዓለም የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በገዛ ራሳችንና በማንነታችን ላይ ያነጣጠረ ቅጥ ያጣ የዘረኝነት ጥላቻ እንዳለ ፣ በንፁሀን ዜጎች በግፍ መገደልና እንዲሁም የተሰፉ፣ የብልጽግናና የአንድነት ምልክት በሆኑት ሐውልቶቻችን ላይ በተደረገው የማፍረስ ተግባር አዝነናል ። ምን ነው? የኦሮሞ ፈርጥ መሪዎቻችንን እነ ታደሰ ብሩን ፣ ጃጋማ ኬሎን ፣ ዋቅጂራ ሰርዳን ፣ ዳዊት አብዲን ፣ ገረሱ ዱኪን ፣ ገበየሁ ጎራውን ወዘተ እረሳናቸው እንዴ ? ለኢትዮጵያ አንድነት የከፈሉት ዋጋ እንዴት ይዘነጋል ? በፖሊቲካ ዘመናቸው ሁሉ እንደነ ሜዤር ቃዲዳ ጉረምሳዬ ከዓፄዎቻችን ጎን የቆሙትና የተካፈሉት ሁሉ እንዴት ይረሳል ?

የኦሮሞ አክራሪ ተገንጣዮች ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. የአቶ ሀጫሉ ሁንዴሳን መገደል ምክንያት በማድረግ የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድን መንግስት ለማደናቀፍና እየተጓዘ ካለበት ሠላማዊ መንገድ ለማስወጣት ሆን ብለው ያደረጉት ሸፍጥ እንደሆነ በግልጽ ያስታውቃል።

የሐውልቶቹ የማፍረስ ወንጀል ጭፍን ጥላቻንና አንድ በሆነችው አገራችን ውስጥ ብዝሀነትና እኩል የዜግነት መብት የተቀረው ኢትዮጵያዊ ሕዝባችን እንዳይኖረው ለማድረግ ነው። ሕዝብን ከፋፍሎ፣ የአንድ ጎጥ የበላይነትን እኩይ ዓላማ ተፈጻሚ በማድረግ ለብዙ ሺ ዘመናት የቆየውን ማህበራዊ ትስስርና ስሪታችንን ለማፍረስ ፣ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ፣ አፍራሽ ሃይሎች ካለማቋረጥ ሌት ተቀን እየሰሩ ይገኛሉ ።

በነጻ የመናገር መብቱ ሊከበርለት ይገባው የነበረው አቶ ሀጫሉ ሁንዴሳ በመገደሉ ምክንያት ተጨማሪና መጠነ-ሰፊ ብጥብጥና የጅምላ ግድያ በመካሄዱ ከመቶ በላይ የንፁሀን ደም ፈሷል አገርና በርካታ ንብረት ወድመዋል ። የአቶ ሀጫሉን ግድያ ምክንያት በማድረግ መገንጠልንና አክራሪ ብሔርተኝነትን ያራመዱ ፣ የኢትዮጵያ አንድነት ምልክቶችን በማፍረስና በማጥቃት አቶ ሀጫሉን አላከበሩትም ፤ ይልቁንስ፣ በስሙ ጥላቻን በማቀንቀን ዝናውና ክብሩን አዋረዱት ። ንፁሃን ዜጎችን በግፍ በመግደል ስብዕናውንና ታሪኩንም አጎደፉት ።

የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ክብር በመጠበቅ ፣ በአድዋና በማይጨው ዘመቻ አገራችንን ከውጭ ወራሪ ሃይሎች በኢትዮጵያዊ ጀግንነት በመከላከል እንደነ ራስ አበበ አረጋይ ፣ የመከላከያ ሚኒስትር ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ፣ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም እና የክቡር ዘበኛ መሪ ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ እንዲሁም ላገራችን አንድነት በጽናት የቆሙትን በርካታ ኦሮሞ አርበኞችና ወታደሮች ዘወትር ልናስባቸውና ልናስታውሳቸው ይገባል።

የአገራችንን ክብርና ሉዓላዊነት እንጠብቅ ። በውጭ አገር መንግስታት ተልዕኮና ድጎማ ሠላማችንን ለማደፍረስና አንድነታችንን ለማናጋት የሚንቀሳቀሱ ጎሰኛ ተገንጣዮች የኦሮሞ እድገት አደናቃፊ ጠላቶች እንጂ የታላቋ ኦሮሞ ፈርጥና አቀንቃኝ መሪዎች አይደሉም ።

የታሪክ አዋቂዎች ፣ ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ እና ራስ መኰንን እንዲሁም ሌሎች መሪዎች አንድነት ፈላጊ ፣ ሕዝብ አሰባሳቢና አስታራቂ እንደነበሩ ያውቃሉ ። ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ በኢትዮጵያችን ኅሠኘነትና የጠቅላይ ግዛቶች ልዩ ጥቅም እንዳይኖር ተግተው ይሰሩ እንደነበር በማወቅ ነው አክራሪዎች ሐውልቶቹን ያፈረሱት ። ግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴና ራስ መኮንን ኦሮሞችን እንዲሁም ሌሎችን ጎሣዎች ከፍ በማድረግ በዘመናዊ ኢትዮጵያ ግንባታና የጋራ ራዕይ በማሳተፍ እኩል ድርሻ እንዲኖራቸው በማድረግ የሚታወቁ እንደነበሩ ሕዝባችን ሊያውቅ ይገባል። ኦሮሞን ወደ ፖሊቲካና ማህብረሰባችን ልብ ውስጥ ስለማስገባታቸው እኔው እራሴ ሕያው ምስክር ነኝ ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩና እንደዚሁም ሌሎች በርካታ ኢትዮጵያዊያንም ምስክሮች ናቸው ። ጽንፈኞች ሊረዱ የሚገባው አንድ ነገር አለ ፤ የራስ መኰንንና የግርማዊ ቀዳማዊ ዓፄ ኃይለ ሥላሴን ትውፊትና ለኢትዮጵያ የነበራቸውን ትልም ለማጨናገፍ መሞከር የሥብዕና ግዝፈትና ገናናነታቸውን ሊቀብረው እንደማይችል ነው ። ትውፊትና ገድላቸው ዘላለማዊ ነውና ።

አባቶቻችን በሕይወት ሳሉ አጥፍተዋል ብለን ለምናስባቸው ጥፋቶች ሁሉ ይቅር መባባል አለብን ። በጋራ እንዳንቆም የሚያግዱንን ልዩነቶቻችንን ሁሉ ማስወገድ አለብን ፤ አለበለዚያ የኛ ትውልድ ጥፋት ለልጆቻችን ይተርፋል ። ዓለም ተቀይራለች ፣ አሁን ያለንበት ጊዜ ከቀድሞ የተለየ ነው።። በሃያ አንደኛው ክፍለ–ዘመን መሠረታዊ የሕልውናና የአኗኗር ዘይቤአችንን የሚቀይሩ ብዙ ፈተናዎች ይገጥሙናል ። ስለዚህም ፣ ሰውነታችንን ፣ እውቀትና ስልጣኔአችንን የሚያዋርዱ ጭፍን ጥላቻንና ድንቁርናን ማሸነፍ ግድ ይለናል ። በማንነቱና በባህላዊ ውርሱ የሚኮራ አንድ ውህድ ቤተሰብ መገንባት አለብን ። የተሻለ መሆን ፣ የተሻለ ማድረግ ፣ መለወጥ እና መበልጸግ እኛን ኢትዮጵያዊያንን አያቅተንም ።

የአቶ ሀጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ግልጽነትና ፍትሐዊነት ባለው ህጋዊ አሰራር መፈታት አለበት ። ገዳዮቹ በግልጽ ችሎትና በሕዝብ ፊት መዳኘት ይገባቸዋል ። የአገር አረጋዊያን ፣ እናቶች ፣ አባቶች ፣ የሀገር ተረካቢ ወጣቶች በአጠቃላይ መላው ኢትዮጵያዊያን የምንማጸናችሁ እጃችንን ለሠላም ፣ ለፍቅርና ለእርቅ እንድንዘረጋ ነው ። አብረን ለለመለመ ተስፋ ፣ ለብልጽግና ፣ ለአንድነትና ለክብራችን ወደፊት እንራመድ ።

ሕዝባችን ፣ ባገር ቤትም በውጭም ፣ በአቶ ሀጫሉ ድንገተኛ ህልፈት ፣ ሂዎታቸውን በጅምላ ግድያ ላጡ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ፣ ለወደመው ንብረት ፣ ለተፈጠረው ቀውስና የሠላም መደፍረስ ፣ ለሕዝባችን ጉሥቁልናና ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ሃዘን ላይ ነን ። የሀጫሉና የብዙ ኢትዮጵያዊያን ሕይወት በከንቱ መጥፋት ቢያሳዝነንም ፣ እንደ አገርና ሕዝብ አንቅቶናል ፤ እያደር የባሱብንን ዘርፈ–ብዙና ውስብስብ ችግሮች ከፊታችን ድቅን አድርጎ እንድናየው አድርጎናል ። የወደፊቱ ተስፋችን አገራችንን በአንድነት እንድንገነባና አኩሪ ታሪክና ባህሎቻችን ተገቢ ክብር እንዲሰጣቸው ነው። ለአገራችንና ለህዝባችን ሠላም፣ ፍቅር፣ ብልጽግናና አንድነት እንመኛለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ፣ ለዕርቅና ለምሕረት በአንድ ላይ እንቁም ። ለልጆቻችን ጽኑ የተስፋ፣ የክብርና የብልጽግና መሰረት እንጣልላቸው ። ኢትዮጵያ አገራችንንና ሕዝባችንን እንታደግ።

“እግዚአብሄር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ”።

ልዑል ኤርሚያስ ሣህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ
የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት ሊቀ መንበር